# መመርያ

## የMONTGOMERY COUNTY የትምህርት ቦርድ

| | |
|---|---|
| **የተዛመዱ ርእሶች፡-** | COF-EA, COF-RA, COH-EA, EEB-RA, GBB-RA, IGO-RA, IGP-RA, JFA, JFA-RA, JGA, JGB-RA, JPC-RA, KGA-RA |
| **ኃላፊነት ያላቸው ቢሮዎች፡-** | ዋና የአካዴሚ መኮንን<br>ዶር. አንድሩ ኤም. ዙከርማን ዋና የሥራ ሀላፊ/Chief Operating Officer<br>የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ |

# በMontgomery County Public Schools የአልኮል፣ ትምባሆ፣ እና የሌላ መድሃኒት መጥፎ አጠቃቀም መከልከል

## A. አላማ

የመመርያው አላማ ከMontgomery County Public Schools (MCPS) ጋር አብሮ በመስራት ለማስተማር፣ ለመማር እና ከአልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች መድሃኒቶች ነፃ የሆነ ሰላማዊ አካባቢ ለመፍጠርና ለመንከባከብ ነው።

## B. ጉዳዩ

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ የአልኮል፣ ትምባሆ እና ሌሎች መድሃኒቶች መጥፎ አጠቃቀም ጎጂ ተፅእኖ በአጠቃላይ ማህበረሰብ፣ እንዲሁም የእነዚህ እና ሌሎች ከፍተኛ ሱሰኛ አድራጊ ኬሚካል ቅመሞችና መድሃኒቶች መጥፎ አጠቃቀም በተማሪዎች አካላዊ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ፣ እና የማሰብና የመመራመር እድገት ላይ ያላቸውን ተፅእኖ ያውቃል። ቦርዱ ከወላጅ/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ ቡድኖች ጋር አብሮ በመስራት፣ ተማሪዎች አካላዊ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ፣ እና አከዴሚያዊ እምቅቻቸውን ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑ፣ እውቀት፣ ውሳኔ-አወሳሰድ ክሂሎቶች፣ እና ጤና-አበልፃጊ ስልቶችን ለመስጠት ያለውን ፍላጎት ያረጋግጣል። እንደ ቀጣሪ/አሰሪ፣ ቦርዱ በተጨማሪ በቦርድ መመርያ GAA፣ *ሓወንታዊ የስራ አካባቢ ራስ-በራስ በሚታደስ ድርጅት ውስጥ* በተቀመጠው መሰረት የሰራተኛ ደህንነት ስርኣቶች፣ እና ከአልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች መድሃኒቶች ነፃ የሆነ የስራ ቦታ ለመንከባከብ የቦርዱን ፍላጎት ያረጋግጣል።

MCPS ከማህበረሰቡ ጋር በመተባበር፣ እንደ አግባቡ፣ የህጋዊና ህገወጥ መድሃኒቶች የሚመለከት መከላከያ ትምህርት፤ እርዳታ፣ ጣልቃገብነት፣ ማስተላለፎች፣ እና ምክር ያቀርባል፤ እናም፣ አስፈላጊ ሲሆን፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች እፆችን የሚመለከቱ ህጎችን፣ የቦርድ መመርያዎችን፣ እና የMCPS ደንቦችን በሚጥሱት ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል።

## C. አቋም

የMCPS ሰራተኞችና ተማሪዎች የፌደራል፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ ህጎችን አጥብቀው እንዲያከብሩና በአፈፃፀማቸው፣ ስራዎቻቸው፣ እና ትምህርት አሰጣጣቸው የአልኮልን፣ ትምባሆን፣ ወይም የሌሎች መድሃኒቶች መጥፎ አጠቃቀም እንዳያደፋፍሩ ወይም እንዳይፈቅዱ ይጠበቅባቸዋል።

ቦርዱ የአልኮል፣ ትምባሆ እና የሌሎች መድሃኒቶች ባለቤትነት፣ አጠቃቀም፣ እና ስርጭት ከMCPS ንብረት ለማስወገድ ግዴታ ገብቷል።

በዚህ መመርያ ውስጥ፣ የMCPS ንብረት ማለት ማናቸውም ት/ቤት ወይም ሌላ መገልገያ፣ በMCPS ንብረትነት ያሉ ወይም የሚንቀሳቀሱ፣ የMCPS ኣውቶቡሶች፣ እና ሌሎች የMCPS ተሽከርካሪዎች፣ እና ተማሪዎችን የሚያካትት በMCPS ስፖንሰር የሚደረግ ማናቸውም እንቅስቃሴ የሚካሄድባቸው መገልገያ እና/ወይም ቦታ ማለት ነው። የዚህ መመርያ ኣላማ/ፍላጎት፣ ከስራ ሰኣቶች ውጭ፣ ከMCPS ንብረት ውጭ፣ የMCPS ሰራተኞች ህጋዊ እንቅስቃሴ/ተግባር ለመከልከል ኣይደለም።

1. *መገናኛ እና ትምህርት*

   a) MCPS ሰራተኞችን፣ ተማሪዎችን፣ እና ወላጅ/ኣሳዳጊዎችን ስለ ቦርድ መምርያዎች፣ የMCPS ደንቦች፣ እና ለማስተማር፣ ለመማር፣ እና ለመስራት ከኣልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች መድሃኒቶች ነፃ የሆነ ሰላማዊ ኣካባቢ ለመፍጠር የተተለሙ ኣስፈላጊ ህጎችን ያስታውቃቸዋል።

   b) MCPS ሰፊ፣ በምርምር-የተመሰረተ የጤና ትምህርት ስርኣተትምህርት፣ ከኤሌመንታሪ ክፍሎች ጀምሮ፣ ለተማሪዎች ኣዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል። ስርኣተትምህርቱ በኣልኮል፣ ትምባሆ፣ እና በሌሎች መድሃኒቶች ኣጠቃቀም ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ታሳቢዎች፤ የኣልኮል፣ ትምባሆ፣ እና የሌሎች መድሃኒቶች መጥፎ ኣጠቃቀም በህብረተሰብ በኣጠቃላይ፤ እንዲሁም የነዚህን እና የሌሎች ኬሚካሎችና መድሃኒቶችን በግለሰቦች ኣካላዊ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ፣ እና የማሰብና የመራመር እድገት ላይ ልዩ ተፅእኖ የሚያደርጉ ታሳቢዎችን ጥያቄ ይመለከታል።

   c) MCPS የመከላከያ ፕሮግራሞችን ያዳብራል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ እና ይደግፋል እናም ተማሪዎች ሌሎች ተማሪዎችን ከኣልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች መድሃኒቶች ጋር ከመነካካት እንዲቆጠቡ እንዲያግዟቸው ያበረታታቸዋል።

2. *ለይቶ ማወቅ እና ድጋፍ*

   a) MCPS፣ ከማህበርሰቡ ጋር በመተባበር፣ የኣልኮል፣ ትምባሆ፣ እና የሌሎች መድሃኒቶችን መጥፎ ኣጠቃቀም ለመከላከል ወይም ህክምና ለማድረግ ለተማሪዎችና ለሰራተኞች ግላዊ እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያራምዳል።

      (1) ለተማሪዎች የሚሰጠው እርዳታ ቀጥተኛ የኣገልግሎቶች ኣቅርቦት ወይም ማስተላለፍ ወደ-፣ እንደኣግባቡ፣ -ት/ቤት ውስጥ የምክር ኣገልግሎቶች፣ -የተማሪ ድጋፍ ድርጅቶች፣ ተለዋጭ ፕሮግራሞች፣ ህዝባዊ ወይም ግላዊ የህክምና ፕሮግራሞች፣ እና ሌሎች የማህበረሰብ ኣገልግሎቶችና ድጋፎች።

      (2) ለሰራተኞች እርዳታ የሚሰጠው በቦርድ *መመርያ* GAA፣ *Positive Work Environment in a Self-Renewing Organization/ኣወንታዊ የስራ ኣካባቢ በራስን-በራስ-የሚያድስ ድርጅት* መሰረት በሰራተኛ እርዳታ ፕሮግራም ኣማካይነት ነው።

   b) MCPS ሰራተኞች ቅር ስለሚሰኙባቸው ባለ-ኣነስተኛ-እድሜ ተማሪዎች ወላጆች ወይም ኣሳዳጊዎች ጋር፣ ምስጢራዊነት በሚከበርበት ዘዴ፣ የሚገናኙባቸው ሂደቶችን ይመሰርታል።

3. *የማህበረሰብ መገልገያዎች ቅንብር*

   MCPS የኣልኮልና ሌሎች መድሃኒቶች ይዞታ፣ ኣጠቃቀም፣ እና ስርጭትን ለመታገል በማህበረሰብ-ኣቀፍ ጥረቶች ይሳተፋል። MCPS ከኣልኮልና ሌሎች መድሃኒቶች መጥፎ ኣጠቃቀም ጋር የተያያዙ ፕሮብሌሞችን የሚመለከቱ የመከላከያ ወይም የህክምና ኣገልግሎቶች መድረሻ ለመጨመር ከማህበረሰብ፣ የማህበረሰብ ጤና ኣቅራቢዎች፣ ወይም ሌሎች የኣካባቢ፣ የስቴት፣ እና የፌደራል ወክል ድርጅቶች ጋር ሽርክናዎችን ይደግፋል ያበረታታልም።

4. የህግ/ደንብ ማስገደድ

a) MCPS ለአልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች መድሃኒቶች ነፃ የሆነ ሰላማዊ የት/ቤት ኣካባቢ ኣጠቃላይ ኣላማ መሳካት ወቅታዊ እርምጃ መወሰዱን በሚከተሉት መንገዶች ያረጋግጣል:-

(1) በMCPS ንብረት ላይ የትምባሆ ሽያጭ ወይም ኣጠቃቀም የመከልከል፣ እናም በMCPS ንብረት ላይ የተማሪዎች ትምባሆ ወይም የትምባሆ ውጤቶች መያዝ የመከልከል እርምጃዎችን ማስገደድ

(2) የኣልኮል እና የሌሎች መድሃኒቶች ወደ MCPS ንብረት ላይ መግባት የመከልከል እርምጃዎችን ማስገደድ

(3) የመሳርያዎችንና የኣመፅን ፕሮብሌሞች ወይም ከኣልኮልና ከሌሎች መድሃኒቶች ኣያያዝ፣ ኣጠቃቀም፣ ወይም ስርጭት ጋር ኣንዳንድ ጊዜ የተያያዘ የኣመፅ ስጋት ጥያቄ ለመቋቋም የጥበቃ/ፀጥታ እርምጃዎች ማቅረብ

(4) ከአልኮልና ሌላ የመድሃኒት መጥፎ ኣጠቃቀም ጋር የተያያዙ ፕሮብሌሞች ጥያቄ ለመቋቋም፣ መከላከል፣ ትምህርት፣ ህክምና፣ እና ህግ ማስከበርን ጨምሮ፣ ከኣካባቢ፣ የስቴት፣ እና የፌደራል ወኪል ድርጅቶች ጋር መተባበር

b) ማንኛውም በMCPS ሰራተኛ የሚፈፀም ከኣልኮል ወይም ሌላ መድሃኒት ጋር የተያያዘ ወይም ያካተተ ህገወጥ እንቅስቃሴ፣ ቦታው፣ የፈለገው ይሁን፣ እስከ እና ወዲያው መሰናበትን ጨምሮ፣ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ መነሻ ይሆናል። ለዲሲፕሊን እርምጃ የወንጀል ፍርድ ኣያስፈልግም።

c) ተማሪዎችን ለሚያካትቱ እንቅስቃሴዎች የዲሲፕሊን መመዘኛዎችና ቅደም-ተከተሎች በቦርድ መመርያ JFA *የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች*፣ እና በMCPS ደንብ JFA-RA፣ *የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች* ተመስርተዋል።

5. የሜሪላንድ ህግ እንደሚጠይቀው፣ የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የኦፖይድ ከመጠን በላይ የመውሰድ ተሞክሮ ይገኛል ተብሎ ለሚገመት ለማንኛውም ተማሪ፣ ወይም በት/ቤት ንብረት ለሚገኝ ሌላ ግለሰብ ኣስቸኳይ የህክምና እንክብካቤ ለማቅረብ ቅደም-ተከተሎችን ያስቀምጣል።

a) የት/ቤቱ ነርስ፣ የት/ቤት የጤና ኣገልግሎቶች ፔርሶኔል፣ እና ሌሎች በት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ወይም ተወካዩ የተለዩ የት/ቤት ፔርሶኔል፣ ናሎክሶን ወይም ሌላ ከመጠን-በላይ-የተወሰደን-ቀልባሽ መድሃኒት ለተማሪ ወይም በት/ቤት ንብረት ለሚገኝ ሌላ ግለሰብ ለመስጠት ስልጣኑ ኣላቸው።

b) የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የሚከተሉትን ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች ኣዳብሮ ተግባራዊ ያደርጋል:-

(1) በኣስኳይ ጊዜ ጥቅም ላይ እንዲውል ናሎክሶን ወይም ሌላ ከመጠን-በላይ የተወሰደን መድሀኒት የሚያወርድ/የሚቀለብስ መድሃኒት ፈልጎ፣ በት/ቤቶች ያከማቻል፤ እና

(2) በየኣመቱ መጀመርያ ላይ ስለዚህ ኣይነቱ ቅደም ተከተሎች/ሂደቶች ወላጆችን ወይም ኣሳዳጊዎችን ያስታውቃል።

## D. ተፈላጊ ውጤቶች

1. ሰላማዊ ኣካባቢ ለማስተማር፣ ለመማር፣ እና ከኣልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ከሌሎች መድሃኒቶች ነፃ በሆነው በMCPS ውስጥ መስራት።

2. የሰራተኛንና የተማሪን መብቶች የሚጠብቁ ደንቦች ማዳበርና መተግበር እናም የሚመለከታቸው ፌደራል፣ ስቴት እና የኣካባቢ ህጎች የቦርድ መመርያዎች፣ እና የMCPS ደንቦችን ማስከበር።

3. ተማሪዎችና ሰራተኞች፣ ስለ የኣልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች መድሃኒቶች መጥፎ ኣጠቃቀም ጎጂ ተፅእኖ በሌለበት፣ እስከ ሙሉ እምቃቸው ለመማርና ለመስራት የሚያስችሉ እውቀት፣ ውሳኔ ኣወሳሰድ ክሂሎቶች፣ እና ጤና-የሚያበለፅጉ ስልቶች እንዲማሩና እንዲታጠቁ ማድረግ።

## E. *ግምገማና ዘገባ*

1. የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ይህን መመርያ የተማሪንና የሰራተኛ ብህትውነት በሚገባ በሚጠብቅ ስርኣት ደንቦችንና ቅደም-ተከተሎችን/ሂደቶችን ያዳብራል።

2. MCPS ስለ ኣልኮልና ሌሎች መድሃኒቶች የሚያካትቱ ኣሳሳቢ ክውነቶች በኣመታዊ የተሰበሰቡ የተማሪ ኣሃዞች ህዝቡንና ቦርዱን ስለዚህ መመርያ ትግባሬ ሁልጊዜ እንዲያውቁ ያደርጋል።

3. ከሰራተኞች ጋር የተያያዙ ክውነቶች በዋና የስራ መኮንን ፅ/ቤት ኣስተዳደርና ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

4. ይህ መመርያ በቦርዱ የመምርያ ግምገማ ሂደት መሰረት ይገመገማል።

***የተዛመዱ ምንጮች፡-*** *Omnibus Transportation Employee Testing Act/ኦምኒበስ የትራንስፖርት ሰራተኛ ኣዋጅ፣ ህዝባዊ ህግ 102-143፣ በ49 Code of Federal Regulations Part 40 ኣማካይነት ኮድ የተደረገ፤ Annotated Code of Maryland, Education Article (ED) §4-124, §7-411-413, §7-426.5, §7-428, §26-103; Annotated Code of Maryland, Criminal Law Article, §5-627; Code of Maryland Regulations 13A.02.04, 13A08.01.08፣ የተዛመዱ የMCPS ሰነዶች፡- መድሃኒቶችና ኣልኮል እና የምርመራ ደንቦች፡- የተቆጣጣሪዎች የእጅ መፅሃፍ፣ የሰራተኛ እርዳታ ፕሮግራም; MCPS K-12 Health Education Curriculum Framework; Just Cause Standards for Bus Attendants and Bus Operators, የትራንስፖርት መምርያ፤ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኣትሌቲክ የእጅ መፅሃፍ፤ የተማሪ-ወላጅ ኣትሌቲክ ተሳትፎ መረጃ*

***የመመርያ ታሪክ፡-*** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 370–90፣ ጁን 12፣ 1990፤ የተሻሻለበት ውሳኔ ቁ. 704–90፣ ኖቨምበር 13፣ 1990፤ የተሻሻለበት ውሳኔ ቁ. 328–13፣ June 13፣ 2013፤ የተሻሻለበት ውሳኔ ቁ. 316-17፣ ጁን 26፣ 2017።

***የተቀዳሚ መመርያ ታሪክ ማስታወሻ፡-*** የፀደቀው በውሳኔ ቁ. 332-70፣ ጁን 9፣ 1970፤ የተሻሻለበት ውሳኔ ቁ. 294-73፣ ኤፕረል 30፣ 1973፤ ዳግመ-ማረጋገጫ ያገኘበት ውሳኔ ቁ. 652-83፣ ጁላይ 25፣ 1983፤ የተሻሻለበት ውሳኔ ቁ. 709-83፣ ኦገስት 9፣ 1983፤ በውሳኔ ቁ.333-86 መሰረት ዳግመ-ቅርፀት የተደረገበት ፣ ጁን 12፣ 1986፤ እና ውሳኔ ቁ. 458-86፣ ኦገስት 12፣ 1986፤ የፀደቀው በውሳኔ ቁ. 517-86፣ ሴፕቴምበር 22፣ 1986፤ ውድቅ የተደረገበት ውሳኔ ቁ. 370-90፣ ጁን 12፣ 1990።